EARLY STAGES

STRONG BEGINNINGS • BRIGHT FUTURES



# የኛ የአሰራር ሂደት

ከዚህ በታች ያለው መረጃ የኧርሊ ስቴጅስን (Early Stages) የአሰራር ሂደት ይዘረዝራል።

## 1 ወደ ኧርሊ ስቴጅስ *(Early Stages)* መላክ *(Referral)*

ማንኛውም ሰው ልጅ ወደ ኧርሊ ስቴጅስ (Early Stages) መላክ ይችላል። ከ 2 ዓመት ከ 8 ወር እስከ 5 ዓመት ከ 10 ወር ለሆኑ ህጻናት ሪፈራል (referrals) እንቀበላለን። ሪፈር (referral) ለማድረግ፤

- የኦንላይን (online) ቅጹን በ www.earlystagesdc.org ድረ-ገጽ ላይ ይሙሉ(ለመላክ (refer) ምርጡ መንገድ)
- የተሟላውን የመላኪያ ቅጽ ወደ referral@earlystagesdc.org በኢሜይል ይላኩ
- በ (202) 698-8037 ይደውሉ
- የተሟላውን የመላኪያ ቅጽ ወደ (202) 654-6079 ፋክስ ያድርጉ

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

## 2 የዕድገት ምመራ (Developmental Screening)

ሪፈራል (referral) ከደረሰን በኋላ፣ እርስዎን፣ ወላጅn; ለአጭር ጊዜ ማጣሪያ እናነጋግርዎታለን። በአካል፣ በስልክ እና በቪዲዮ ጥሪ ማጣሪያ አማራጮችን እናቀርባለን።

በማጣሪያው ወቅት፣ ስለልጅዎ እድገት እና የህክምና ታሪክ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ የዕድሜ እና ደረጃዎች መጠይቅ (Ages and Stages Questionnaire (ASQ)) እንጠቀማለን። ዶክተሮችን፣ አስተማሪዎችን፣ እና የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎችን ጨምሮ የልጅዎን ሌሎች ተንከባካቢዎችን ለማነጋገር ልንጠይቅ እንችላለን። እንደ የሕክምና መዝገቦች እና የግምገማ ሪፖርቶች ያሉ አንዳንድ ሰነዶችን ልንጠይቅ እንችላለን።

እንዲሁም ስለ ልዩ ትምህርት ሪሶርሶች (resources) እንሰጥዎታለን. እነዚህ አስፈላጊ ውሎችን እና በሂደቱ ውስጥ ያለዎትን መብቶች እንዲረዱ ያግዝዎታል።

ከማጣሪያው በኋላ ስለተጨማሪ ግምገማ አስፈላጊነት እንነጋገራለን።

## 3 ግምገማ



የማጣራት ውጤቶችን መሰረት በማድረግ የግምገማ ቀጠሮ ልንይዝ እንችላለን። ግምገማ ልጅዎ ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ መሆኑን ይወስናል። የግምገማው ሂደት የሚጀምረው የእርስዎን ፈቃድ ካገኘን በኋላ ነው። ፍቃድዎ በጽሁፍ የሚሰጡት ፍቃድ ነው።

### የግምገማው ቡድን የሚከተሉትን ሊገመግም ይችላል፤

- መግባባት (Communication) (ንግግር እና ቋንቋ)፤ ልጅዎእንዴት እንደሚናገር፤ እንደሚረዳ፤ እና ቋንቋን እንደሚጠቀም
- የለጋ ዕድሜ ትምህርት (ማሰ፤ ችግርን መፍታት፤ እና የትምህርት ክህሎቶች)፤ እንዴት እንደሚማር እና መረጃዎችን እንደሚጠቀም
- አካላዊ ዕድገት (መንቀሳቀስ፤ የጣቶች እንቅስቃሴ ክህሎቶች (Fine Motor Skills)፤ እና የስሜት ህዋሳትን ማካሄድ)፤ ልጅዎ እንዴት እንደሚንቀሳቀስ፤ እንደሚያይ፤ እንደሚሰማ፤ ትንንሽ መስሎችን እንዴት እንደሚተቀም፤ የስሜት ህዋሳቱን እንዴት እንደሚተቀም
- ማህበራዊ ስሜታዊ ዕድገት፤ ልጅዎ ከሌሎች ጋር እንዴት እንደሚዛመድ እና እንዴት ባህሪያቸው የዕለት ተዕለት ኑሯቸው ላይ ተጽዕኖ እንደሚኖረው

### ግምገማው የሚከተሉትን ያካትታል፤

- ቃለ-መጠይቅ እና ጥያቄዎች
- የመስማት እና የማየት ምርመራ
- መማር፤ መናገር፤ መንቀሳቀስ የመሳሰሉትን ክህሎቶች መመርመር
- ልጅዎን በማየት መከታተል
- የልጅዎን የህክምና፤ የማህበራዊ እና የቤተሰብ ታሪኮች መገምገም

እርስዎ የልጅዎ የግምገማ ቡድን ጠቃሚ አባል ነዎት። ጥያቄዎችን እንድትጠይቁ እና ስጋቶችን፣ ግቦችን እና ስለልጅዎ መረጃ እንዲያካፍሉ እናበረታታዎታለን።

## 4 የብቁነት ስብሰባ

በብቁነት ስብሰባ ወቅት፣ ቡድኑ የልጅዎን የግምገማ ውጤቶች ይገመግማል። አንድ ላይ፣ ልጅዎ ለልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ መሆኑን እንወስናለን። በ ዕክል ያለባቸው ሰዎች ህግ (Individuals with Disabilities Act (IDEA)) መሰረት ልጅዎ በ አይዲኢኤ (IDEA-defined) የተገለጸ ትምህርታቸው ላይ ተፅእኖ የሚያደርግ ዕክል ካለባቸው ለአገልግሎት ብቁ ይሆናሉ።

ልጅዎ ብቁ ከሆነ፣ ለአገልግሎቶች ብቁ ይሆናሉ፣ እና ቡድኑ በአይኢፒ (IEP) ስብሰባ ወቅት የግለሰብ የትምህርት ፕሮግራም (አይኢፒ (IEP)) ያዘጋጃል።

ልጅዎ ብቁ ካልሆነ፣ ለአገልግሎቶች ብቁ አይደሉም፣ እና ሂደቱ ያበቃል። ስለልጅዎ እድገት ጠቃሚ መረጃ ይተውልዎታል። ልጅዎን እንዴት የበለጠ መደገፍ እንደሚችሉ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ መስጠት እንችላለን።

## 5 የአይኢፒ (IEP) ስብሰባ

*(ግላዊ የትምህርት መርሃ-ግብር (Individualized Education Program))*

አይኢፒ (IEP) ልጅዎ በትምህርት ቤት ስኬታማ እንዲሆን የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን የሚዘረዝር የጽሁፍ ሰነድ ነው።

አይኢፒ (IEP) አገልግሎቶች ሊጀምሩ የሚችሉት ፈቃድ ከሰጡ በኋላ ብቻ ነው። ፈቃድ ላለመስጠት ወይም ፈቃድን በማንኛውም ጊዜ መልሰው ለመውሰድ መምረጥ ይችላሉ። እርስዎ እና የልጅዎ ቡድን አገልግሎቶች መቼ መጀመር እንዳለባቸው ይወስናሉ። ልጅዎ ከሶስት አመት በታች ከሆነ፣ አይኢፒ (IEP) እስከ ሶስተኛ ልደታቸው ድረስ መጀመር አይችልም።

የልጅዎ ት/ቤት ቡድን አይኢፒ ን (IEP) ቢያንስ በዓመት አንዴ ከእርስዎ ጋር ይገመግማል።

### አይኢፒ (IEP) አገልግሎቶች

በ አይኢፒ (IEP) ላይ ያሉ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ልዩ ትምህርትን ያካትታሉ። ልዩ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርቱን ከልጅዎ ፍላጎቶች ጋር ያስተካክላል።

አገልግሎቶቹ ልዩ ተዛማጅ አገልግሎቶችንም ሊያካትቱ ይችላሉ። ተዛማጅ አገልግሎቶች የክፍል ትምህርትን ይደግፋሉ። ለምሳሌ፣ ልጅዎ የንግግር-ቋንቋ አገልግሎቶችን፣ የሙያ ህክምና ወይም የባህሪ ድጋፍ አገልግሎቶችን ሊቀበል ይችላል።



### የአገልግሎቶች ዕቅድ (SERVICES PLAN)

ልጅዎን በግል ወይም በሃይማኖታዊ ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ ከመረጡ የአገልግሎት እቅድ ማዘጋጀት እንችላለን። የአገልግሎት እቅድ በአይኢፒ (IEP) ላይ ያሉትን ሁሉንም አገልግሎቶች አይሰጥም። የልጅዎን ፍላጎቶች ሙሉ በሙሉ ላያሟላ ይችላል። የዲሲፒኤስ (DCPS) ጉዳይ አስተዳዳሪ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የአገልግሎቶቹን እቅድ ከእርስዎ ጋር ይገመግማል።

## 6 የትምህርት ቤት ምዝገባ

የኧርሊ ስቴጅስ (Early Stages) ሂደት በዲሲፒኤስ (DCPS) ት/ቤት ለመመዝገብ ዕድል በመስጠት ያበቃል። በመጀመሪያ በአካባቢዎ ያለ ት/ቤት የልጅዎን  አይኢፒ (IEP) ተግባራዊ ማድረግ እንደሚችል እናረጋግጣለን። ይህ ት/ቤት ቦታ ካለው የምንሰጠው ት/ቤት ነው። የአካባቢው ት/ቤት አማራጭ ካልሆነ፣ አይኢፒን (IEP) ተግባራዊ ሊያደርግ የሚችል ቀጣዩን ቅርብ ት/ቤት እናቀርባለን። እንደ ወንድም የእህት ምርጫ እና ተደራሽነት ያሉ ሌሎች ነገሮችን ልንመለከት እንችላለን።

አገልግሎቶችን ለማግኘት ልጅዎን ትምህርት ቤት ማስመዝገብ አለብዎት። የመጀመሪያ ደረጃዎች በዲሲፒኤስ (DCPS) ብቻ መመዝገብ ይችላሉ። ልጅዎን በህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ካስመዘገቡ፣ አይኢፒውን (IEP) ማስተላለፍ ይችላሉ። ልጅዎን በግል ወይም በሃይማኖት ትምህርት ቤት ካስመዘገቡ፣ በምትኩ የአገልግሎት እቅድ መጠየቅ ይችላሉ።



### የስረዛ ፖሊሲ

ኧርሊ ስቴጅስ (Early Stages) የመጀመሪያ ደረጃዎች ጥብቅ የግምገማ ጊዜዎችን ለመከተል በህግ ይገደዳሉ። ያመለጡ ቀጠሮዎች ቤተሰቦችን በጊዜው የማገልገል ችሎታችንን ይነካሉ። ቀጠሮ መሰረዝ ካለብዎት፣ እባክዎን በተቻለ ፍጥነት ለ ኧርሊ ስቴጅስ (Early Stages) ያሳውቁ። ከ24 ሰዓት ባነሰ ማስታወቂያ መሰረዝ እንደ ያመለጠ ቀጠሮ ይቆጠራል። ይህ የልጅዎ ጉዳይ እንዲዘጋ ሊያደርግ ይችላል።

*(202) 698-8037* | *info@earlystagesdc.org* | *www.earlystagesdc.org*